ሕብባማ
EBA

# ተሟጋች
# TEMUAGACH

በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የሚዘጋጅ

1ኛ ዓመት ቁጥር 11 ጥቅምት 2001

## ርዕሰ አንቀጽ

### የዳኝነት ነፃነት - የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱ ዋና ምሰሶ

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሁነኛና ዋና ዋና ምሰሶዎች አሉት። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት እየተጣለ ነው ለማለት ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ፣ አማራጭ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲ አውጥተው በምርጫው በነፃነት የሚወዳደሩ ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ በምርጫ አማካይነት በሕዝብ ሙሉ ፍላጐት የሚቆም መንግሥት፣ ነፃ ውድድር የሰፈነበት የኢኮኖሚ ሥርዓት፣ ነፃ፣ ገለልተኛና ጠንካራ የዳኝነት ሥርዓት መኖር አለበት።

በራሱ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ በራሳቸው የሚቆሙ፣ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና የሚተራረሙ የሕግ አውጭ፣ የሕግ ተርጓሚና የሕግ አስፈፃሚ አካላት በሚኖራቸው የእርስ በርስ ቁጥጥር ሂደት ወሳኝ ሚና የሚጫወት «የመንግሥት አራተኛው ክንፍ» በመባል የሚታወቀውና «የሕዝብ ዓይንና ጆሮ»፣ «የሕዝብ ዘብ» ሆኖ የሚያገለግል ነፃና ገለልተኛ ፕሬስ ያስፈልጋል።

በተለይም አስፈፃሚ አካሉ ልጓም የሌለው ፈረስ እንዳይሆንና በሕዝብ ላይ አምባገነን ሆኖ እንዳይወጣ በመቆጣጠር፣ የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን በማስከበር በኩል የዳኝነት ሥርዓቱ ወሳኝ ሚና አለው።

የዳኝነት ሥርዓቱ በሰው መሠረታዊ መብቶች፣ በሰው ሕይወት፣ በንብረት ባለቤትነት ላይ የሚወስን እንደመሆኑ ነፃ ከመሆኑና ከጥንካሬው ጐን ብስለትን የተላበሰ ሊሆን ይገባል። ይህንንም ለማረጋገጥ ነው በዚህ እትም የሰፈረው «የዳኝነት ነፃነት መሠረታዊ መርሆዎች» በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በውሣኔ ቁጥር 40/32 ኖቬምበር 29 ቀን 1985፣ በውሣኔ ቁጥር 40/46 ዲሴምበር 13 ቀን 1985 የፀደቀውን ለንባብ ያበቃው።

በአገራችንም ከሕገ-መንግሥቱ አንስቶ የዳኝነት ነፃነትን የሚመለከቱ ሕጐች ወጥተዋል። የሕጐቹ መውጣት አንድ ነገር ሆኖ እነዚህ ሕጐች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሰፈሩ መርሆዎች አንጻር መገምገማቸውና ተግባራዊነታቸውም መቃኘቱ ወቅታዊ ጥያቄ ሆኗል። ዳኝነት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንድ አብይ ምሰሶ በመሆኑና ለሕጋዊነትና ለዜጐች መብት መከበር አስፈላጊነቱ አጠያያቂ ባለመሆኑ ለዳኝነት ነፃነት መከበር ሁሉም ዜጐች፣ በተለይም በሕግ ሙያ የሰለጠኑ፣ በመስኩም በዳኝነት፣ በጥብቅናና በዐቃቤ ሕግነት የተሰማሩ ሁሉ ብዙ ይጠበቅባቸዋል። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ዕውን ሊሆኑ የሚችሉት የዳኝነት ሥርዓቱ ከአስፈፃሚ አካሉ ነፃ ሲሆንና ሕጋዊነትን የማስከበር አቅም ሲኖረው ብቻ ነው።

## ነፃ የሕግ አገልግሎት የሰጡ ጠበቆች ተሸለሙ

ገንዘብ ከፍለው ጠበቃ ለማቆም ለማይችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት የሰጡ 41 ጠበቆችና ሌሎች የሕግ ባለሞያዎች ተሸለሙ።

አክሽን የባለሞያዎች ማኀበር ለሕዝብ (አፐአፐ) ኅዳር 9 ቀን 2001፣ ከሰዓት በኋላ፣ ከ9 ሰዓት ጀምሮ በጊዮን ሆቴል፣ ሳባ አዳራሽ ባካሄደው ሥነ-ሥርዓት ከሽልማቱ በተጨማሪ ነፃ የሕግ አገልግሎትንና ጠቀሜታውን በተመለከተ ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቦ ውይይት ተደርጐበታል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በካሣ ክርክር ረታ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የ150,000 ብር ካሣ በአውቶቡስ አደጋ አንድ እጅ እና እግሩን ላጣው ተጐጂ እንዲከፈለው አስፈረደ።

ተጎጂው አቶ ፈጠነ ንጉሴ የካቲት ወር በ1995 በደረሰባቸው የአውቶቢስ ግጭት አንድ እጃቸውን እና እግራቸውን ያጡ ሲሆን የአንበሳ የከተማ አውቶቢስ ድርጅት ኢንሹራንስ ሰጪ የሆነው የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ የ30,000 ብር ካሣ ለተጎጂው ቢከፍልም የብሩ መጠን ተጎጂው ለህክምናው የሚያወጣውን ወጪ እንኳን የሚሸፍን አልነበረም።

በዚህ ምክንያት አቶ ፈጠነ ወደ ኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በመቅረብ ሁኔታውን ከአስረዱ በኋላ ነፃ የሕግ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ጠይቀው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ለተጐጂው ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጡ የሕግ ጠበቃ አቶ ምህረተአብ ልዑልን አቁሞላቸው ክርክሩ ሲካሄድ ቆይቷል።

ጠበቃው አቶ ፈጠነን በመወከል አንበሳ የከተማ አውቶቢስ ድርጅትን ተጨማሪ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ክስ መስርተው ተጨባጭ እና አሳማኝ መከራከሪያዎችን በማቅረብ ለ3 ዓመት የክስ ሂደቱን ተከታትለዋል። በመጨረሻም ክሱን ሲከታተል የነበረው ፍ/ቤት ተከሳሽ ብር 150,000 ካሣ ለከሳሽ እንዲከፈለው ውሳኔ ሰጥቶ መዝገቡ ተዘግቷል።

በውሣኔው መሠረት ብር 150,000 የካሳ ክፍያ የያዘውን የባንክ ደብተር የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ ለተጎጂው አስረክበዋል።

## በሕግ ጉዳዮች ላይ ወርሃዊ ውይይት ተጀመረ

ላንቻ በስተጀርባ በሚገኘው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተከታታይ የሕግ ትምህርት ማዕከልና የጠበቆች ክበብ ውስጥ በወቅታዊ የሕግ ጉዳዮች ላይ ወርሃዊ ውይይት ተጀመረ።

ውይይቱ የሚመራው በአገር ውስጥ ባሉ እና ከውጭ አገር በሚመጡ የሕግ ምሁራን ሲሆን እስካሁን የኢትዮጵያ የፍትህ ሥርዓት ዕድገት፣ የአገር ሉዓላዊነት እና በሌሎች አገሮች ላይ የሚወሰድ የኃይል እርምጃ፣ በዓለም አቀፋዊ ግልግል ሥርዓት፣ የንግድ ድርድር፣ በንግድ ድርጅቶች ውስጥ የሚፈፀመው ወንጀሎች እና በዓለም አቀፋዊ የግብር ሥርዓት በሚሉ ርዕሶች ላይ ውይይቶች ተደርገዋል።

## ከኦባማ መመረጥ በኋላ የአፍሪካ ዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ ወደቀ

አፍሪካውያን የኦባማ ማሸነፍ አስደስቷቸዋል። ነገር ግን በአሜሪካ የመጀመሪያ አፍሪካዊ አሜሪካዊ በምድረ አሜሪካ መሪ ሆኖ መመረጥ አፍሪካ እየተከተለች ያለችውን የዴሞክራሲ ሁኔታ በተመለከተ አወዛጋቢ ጥያቄዎች እየተነሱ ናቸው።

የምርጫው ውጤት እንደታወቀ በአህጉሪቷ አገሮች ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የኦባማ ማሸነፍ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ወቅታዊ ጉዳይ

# የዳኝነት ነፃነት መሠረታዊ መርሆዎች

**ስለወንጀል መከላከል እና ስለወንጀል ድርጊት ፈጻሚዎች አያያዝ ለመነጋገር ኦገስት 26 ቀን እስከ ሴፕቴምበር 6 ቀን 1985 ሚላን ከተማ በተካሄደው ሰባተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባዔ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 40/32 ኖቬምበር 29 ቀን 1985 በውሳኔ ቁጥር 40/46 ዲሴምበር 13 ቀን 1985 ዓ.ም. አፅድቋል።**

የዓለም ሕዝቦች ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተቋቋመበት ቻርተር ድንጋጌ መሠረት የሰብአዊ መብቶችንና የመሠረታዊ ነፃነቶችን መከበር ለማበረታታትና ለማራመድ እንዲቻል ፍትሕ የሚሰፍንባቸውን ሁኔታዎች ለመመሥረት ቁርጠኝነታቸውን ያረጋገጠ ስለሆነ፣

ሁሉ-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ መግለጫ ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑን፣ ጥፋቱ በፍርድ ቤት እስኪረጋገጥ ድረስ ከወንጀል ነፃ ተደርጎ የመወሰድ መብትንና በሕግ በተቋቋመ፣ ሥልጣን ባለው፣ ነፃና አድሎአዊ ባልሆነ ፍርድ ቤት ትክክልና ግልጽ ዳኝነት የማግኘት መብትን የሚደነግጉ መርሆዎችን በተለይ በማካተቱ፣

ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባሕል መብቶች ጥበቃ ስምምነትና ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ጥበቃ ስምምነት በእነዚህ መብቶች ለመጠቀም ዋስትና ስለሚሰጥና በተጨማሪም የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ጥበቃ ስምምነት ያላንዳች መዘግየት ዳኝነት የማግኘት መብትን የሚያረጋግጥ በመሆኑ፣

በእነዚህ መርሆዎች በተገለጹት ዓላማዎችና በተግባር እየተፈጸሙ ባሉ ድርጊቶች መካከል ልዩነቶች በየጊዜው ስለሚከሠቱ፣ በእያንዳንዱ አገር የፍትሕ አደረጃጀትና አስተዳደር በእነዚያ መርሆዎች መመራት ያለበት በመሆኑና እነዚያን መርሆዎችም በተግባር ለመተርጎም ጥረት መደረግ ያለበት በመሆኑ፣

የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን የሚመለከቱ ደንቦች ዳኞች ተግባራቸውን በእነዚያ መርሆዎች በመመራት ለማከናወን የሚያስችሉ መሆን ስላለባቸው፣

ዳኞች በዜጎች ሕይወት፣ ነፃነት፣ መብት፣ ግዴታና ንብረት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ፣

ወንጀልን ስለመከላከልና የወንጀል ድርጊት ፈጻሚዎችን አያያዝ ለመወሰን የተጠራው ስድስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ በ16ኛ ውሳኔው የወንጀል መከላከልና ቁጥጥር ኮሚቴ የዳኝነት ነፃነትን፣ የዳኞችንና የዐቃቤ ሕጎችን አመዳደብ፣ ሙያዊ ሥልጠናንና አቋምን የሚመለከቱ መመሪያዎችን በዝርዝር ማውጣትን በተግባር ቅደም ተከተል አጀንዳው እንዲይዝ ጥሪ ማድረጉን በመገንዘብ፣

ስለሆነም የፍትሕ ሥርዓትንና የዳኞችን አመዳደብ፣ ሥልጠናና ሥነ - ምግባር በሚመለከት ዳኞች ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ተገቢ ስለሆነ፣

አባል አገሮች የዳኝነት ነፃነትን የማረጋገጥና የማራመድ ተግባሮቻቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ እንዲረዱባቸው የወጡት የሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፤ መንግሥታትም እነዚህ መርሆዎች በብሔራዊ ሕጎቻቸው እንዲደነገጉና በተግባርም እንዲተረጎሙ፣ እንዲሁም በዳኞች፣ በሕግ ባለሙያዎች፣ በሕግ አስፈጻሚና በሕግ አውጭ የመንግሥት ዘርፎች አባላትና በሕዝቡ በአጠቃላይ ትኩረት እንዲሰጣቸው ማድረግ አለባቸው። መርሆዎቹ የተዘጋጁት ባለሙያ ዳኞች እንዲመሩባቸው ሲሆን ባለሙያ ያልሆኑ ዳኞች በሚመደቡበት ቦታም እንዲሁ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## የዳኝነት ነፃነት

የዳኝነት ነፃነት በመንግሥት ዋስትና ይሰጠዋል፣ በአገሩ ሕገ - መንግሥትም ይደነገጋል። መንግሥታዊ የሆኑና መንግሥታዊ ያልሆኑ ሌሎች ተቋማት የዳኝነት ነፃነትን ያከብራሉ፣ ይጠብቃሉም።

ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸውን ጉዳዮች በመመርመር በምንም ዓይነት ምክንያት ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚመጡ ቀጥታ ወይም ቀጥታ ላልሆኑ ተፅዕኖዎች፣ ማባበያዎችም፣ ግፊቶች፣ ማስፈራራቶችና ጣልቃ ገብነቶች ሳይበገሩ ያለአንዳች ገደብ በፍሬ ነገርና በሕግ ላይ በመመሥረት ውሳኔ (ፍርድ) ይሰጣሉ።

ፍርድ ቤቶች ዳኝነትን በሚጠይቁ ጉዳዮች ሁሉ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል። ለውሳኔ (ለፍርድ) የቀረቡላቸውን ጉዳዮችም በሕግ በተደነገገው መሠረት አይቶ የመወሰን ብቸኛ ሥልጣን አላቸው።

በፍርድ ሂደት ማንኛውም አግባብ ያልሆነ ወይም የማይፈለግ ጣልቃ ገብነት አይኖርም፣ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎችም (ፍርዶችም) እንደገና አይከለሱም። ይህ ግን አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድን (ውሳኔን) በሕግ በተደነገገው መሠረት እንደገና የማየት፣ የተሰጠ ቅጣትን ለመቀነስ ወይም ለመሠረዝ (ለማንሳት) ያላቸውን ሥልጣን የሚገድብ አይደለም።

ማንኛውም ሰው በሕጋዊ ሥርዓት በሚመሩ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች የመዳኘት መብት አለው። የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን ወይም ችሎቶችን ሥልጣን በመጋፋት በሕግ ባልተደነገገ ሥነ - ሥርዓት የሚመሩ ችሎቶች አይመሠረቱም።

የዳኝነት ነፃነት መርህ ዳኞች የዳኝነት ሥራዎችን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ እንዲያ ከናውኑና የተከራካሪ ወገኖችን መብቶች እንዲያከብሩ የሚጠይቅ ነው።

እያንዳንዱ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን እንዲችሉ በቂ አቅም የመገንባት (የማዘጋጀት) ግዴታ አለበት።

ወቅታዊ ጉዳይ

## ሀሳብን በነፃ የመግለጽና በነፃ የመደራጀት መብቶች

የዳኝነት (የፍትህ) አካላት አባላት እንደሌሎች ዜጎች በሁሉ አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ መግለጫ ድንጋጌ መሠረት ሀሳባቸውን በነፃ የመግለጽ፣ የእምነት፣ በማኅበር የመደራጀትና የመሰብሰብ መብት አላቸው:: ሆኖም ዳኞች ምንጊዜም ራሳቸውን የዳኝነትን ክብርና ነፃነትን ለሚያስጠብቅ እና እንዲሁም ከአድልዎ ነፃ ለሆነ ሥርዓት ማስገዛት አለባቸው::

ዳኞች ጥቅማቸውን ለማስከበር፣ የሙያ ችሎታቸውን ለማሻሻልና የዳኝነት ነፃነትን ለመጠበቅ በማኅበር ለመደራጀት ወይም የሌሎች ማኅበራት አባላት ለመሆን ነፃ ናቸው::

## የሙያ ችሎታ፣ አመዳደብና ሥልጠና

በዳኝነት ሥራ የሚመደቡ ሰዎች ክብራቸውን የጠበቁና ተገቢው ሥልጠና ያላቸው ወይም በሕግ ሙያ የሰለጠኑ ይሆናሉ:: ማናቸውም ዳኞች የሚመደቡበት ስልት (ሥርዓት) ተገቢ ያልሆነ ፍላጎትን ለማሟላት ከሚደረግ ሹመት ነፃ ይሆናል:: በዳኞች አመዳደብ ጊዜ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በብሔር ወይም በማኅበራዊ ምንጭ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በአቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ማድረግ አይፈቀድም:: ሆኖም ለዳኝነት ሥራ የሚመለከተው አገር ተወላጅ ብቻ እንዲመደብ ማድረግ ልዩነት እንደማድረግ አይቆጠርም::

## ዳኞች አገልግሎት የሚሰጡባቸው ሁኔታዎችና የአገልግሎት ጊዜ

የዳኞች የአገልግሎት ጊዜ፣ በሥራቸው ነፃ መሆናቸው፣ ሊሰጣቸው የሚገባው ዋስትና፣ በቂ ክፍያ የማግኘታቸው ሁኔታ፣ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ሁኔታዎች፣ የጡረታ መብቶቻቸውና በጡረታ የሚገለገሉበት የዕድሜ ጣራ በቂ የሕግ ዋስትና ያገኛሉ::

የሚሾሙም ሆኑ የሚመረጡ ዳኞች በጡረታ የሚገለሉበት ጊዜ ደርሶ በጡረታ ካልተገለሉ ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ጨርሰው ካልተሰናበቱ በስተቀር በሥራቸው ላይ ለመቆየት ዋስትና አላቸው::

የዳኞችን ዕድገት የሚመለከት ሥርዓት ካለ ዳኞች ዕድገት የሚያገኙት ተጨባጭ በሆኑ መመዘኛዎች በተለይም በችሎታቸው፣ በልምዳቸውና ለሥራው ባላቸው ታማኝነት ነው::

ጉዳዮችን በፍርድ ቤቱ ተመድበው ለሚሠሩ ዳኞች የመምራት ሁኔታ የፍርድ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ጉዳይ ነው::

## በሥራ አጋጣሚ የተገኘ ምሥጢርን ስለመጠበቅና በኃላፊነት ስላለመጠየቅ

ዳኞች በግልጽ የፍርድ ሂደት የተገኙት ካልሆነ በስተቀር ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ከሚቀርቡላቸው ክርክሮችና ምሥጢራዊ ሰነዶች ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን ነገሮች ሁሉ በምሥጢር የመያዝ ግዴታ አለባቸው፤ በእነዚህ ጉዳዮች ላይም ምሥክርነት እንዲሰጡ አይገደዱም::

ብሔራዊ ሕግ በሚደነግገው መሠረት በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያት ማናቸውም የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ የመጠየቅ፣ ይግባኝ የማቅረብና ከመንግሥት ካሣ የመጠየቅ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዳኞች የዳኝነት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ወይም አላግባብ ሳይፈጽሙት በቀረ ጉዳይ የገንዘብ ካሣ እንዲከፍሉ የፍትሐ ብሔር ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም::

## ዲሲፕሊን፣ ማገድና ማሰናበት

ዳኞች የዳኝነት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወይም የሙያ ግዴታቸውን በሚወጡበት ጊዜ በሚፈጽሟቸው ድርጊቶች የሚቀርብ ክስ ወይም ቅሬታ አግባብ ባለው ሥነ ሥርዓት በፍጥነትና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲታይ ይደረጋል:: ዳኞችም የቀረበባቸው ክስ ወይም

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

**ተሚጋች** - በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኀበር በየሁለት ወር የሚታተም

ስልክ : 251-11-553-0122

ፖ.ሣ.ቁ. : 700

ፋክስ : 251-11-515-2047

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሜይል : eba@ethionet.et

ዌብሳይት : www.ethiopian-bar.org

## ነፃ የሕግ አገልግሎት. . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

በዚሁ ሥነ-ሥርዓት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የአክሽን የባለሞያዎች ማኀበር ለሕዝብ የቦርድ ሰብሳቢና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት ተባባሪ ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ ሲሆኑ ሰብዓዊ መብትን በማስከበር፣ በተለይም የፍትህን አገልግሎት የመክፈል አቅም ለሌላቸው በማዳረስና ነፃ የሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት የጠበቆችን ሚና አውስተው ጠበቆች አገልግሎታቸውን አጠናክረውና አስፋፍተው እንዲቀጥሉ አሳስበዋል::

ቀጥሎም በአቶ ታምሩ ወንድም አገኘሁ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያዎች ማኀበር ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት ነፃ የሕግ ምክርና ጥብቅና አገልግሎት አስፈላጊነት፣ በኢትዮጵያ ጠበቆች የመክፈል አቅም ለሌላቸው ዜጎች በዓመት የ50 ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጡ የሕግ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ አስታውቀዋል:: በተጨማሪም ለድሆች ነፃ የሕግ አገልግሎት በመስጠት የሌሎች አገሮች ልምድ የተካተተበት ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቧል:: በኢትዮጵያ ሕጉ ቢኖርም እስከአሁን ተፈፃሚ አልሆነም በማለት ጥናታዊ ጽሑፉ ጠቁሟል::

በዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ በተደረገ ውይይት ኅብረተሰባችን ካለበት ድህነት አንፃር በኢትዮጵያ በተበታተነ መልክ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ልዩ ልዩ ድርጅቶች የሚሰጡ ነፃ የሕግ አገልግሎቶች በአንድ ተቋም ሥር ተሰባስበው አገልግሎቱ ከአዲስ አበባም ወጣ ብሎና ተጠናክሮ ሊሰጥ እንደሚገባ ተሰምሮበታል::

በጥናታዊ ጽሑፉ ላይ ከተደረገው ውይይት ቀጥሎ በአዲስ አበባ እና በሐረሪ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ ክልሎች ነፃ የሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት የሰጡ ጠበቆችና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የአፕአፕ ማዕከሎች የመዳሊያና የዋንጫ ሽልማትና የምሥክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል::

በመጨረሻም አቶ ደሳለኝ በርሄ፣ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ነፃ የሕግ አገልግሎት የመክፈል አቅም ለሌላቸው ለመስጠት ተነሳሽነትን ወስደው የፍትህ ተደራሽነትን ለማስፋት አስተዋፅኦ በማድረጋቸው ባለሙያ ተሸላሚዎችን አመስግነዋቸዋል:: በተጨማሪም የፌደራል ፍ/ቤቶች ለዚህ ነፃ የሕግ አገልግሎት ከጐን እንደሚቆሙ ገልፀዋል::

ወቅታዊ ጉዳይ

## የዳኝነት ነፃነት. . .

(ከገጽ 3 የዞረ)

ቅሬታ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲታይ የማስደረግ መብት አላቸው:: በዳኞች በራሳቸው በሌላ አኳኋን ካልተጠየቀ በስተቀር በቀረበው ክስ ወይም ቅሬታ ላይ የሚካሄደው ምርመራ ውጤቱ ከመታወቁ በፊት ግልጽ አይደረግም::

ዳኞች ከምድብ ሥራቸው የሚታገዱት ወይም የሚሰናበቱት በችሎታ ማጣት ወይም በባሕርይ ጉድለት ምክንያት ግዴታቸውን ለመወጣት የማይችሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው::

የዲሲፕሊን (የሥነ ሥርዓት) ጉድለትን፣ ከሥራ ማገድንና ማሰናበትን የሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች መደበኛውን የዳኝነት አሠራር ሥርዓት በመከተል ይወሰናሉ::

ዲሲፕሊን ጉድለት የሚያስጠይቁ እርምጃዎች፣ ከሥራ ማገድና ማሰናበት በነፃ አካል መታየት አለባቸው:: ይህ መርህ ግን የመጨረሻው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም በሕግ አውጪው አካል በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

## ከኦባማ መመረጥ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከራሳቸው አገር የዴሞክራሲ ችግር ጋር በማወዳደር ሀዘናቸውን እየገለፁ ይገኛሉ::

የናይጄሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የነበሩትና አሁን የአገሪቷ የምርጫ ኮሚቴ አባል የሆኑት ሚስተር ቦልጂ አኪንዎሚ እንዳሉት «መግለጫው እንደተሰጠ ተንበርክኬ አለቀስኩ:: በመጀመሪያም እግዚአብሔር ላሳየኝ ደስታ፣ ቀጥሎም አዝኜ ለአገሬ አለቀስኩ» በማለት ገልጠዋል::

የነሚስተር አኪንያሚ ድርጅት በአፍሪካ በሕዝብ ብዛት ለምትታወቀው አገራቸው ናይጄሪያ ዴሞክራሲን አንፃረው ለማውጣት ውጣ ወረድ ያለው ትግል እየታገሉ ቢሆንም ፕሬዚዳንት ኡማሩ ያራድ ኢኤ. የኤፕሪል 2007 ያሸነፉበት ምርጫ እስከአሁን በጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲፀድቅ ቀርቧል:: በአሁኑም ሰዓት እንደሚታወቀውም ፍ/ቤቱ ውሳኔውን ላልተወሰነ ጊዜ አራዝሟል::

ተመሳሳይ ጥያቄ በኬንያና በዚምባብዌ ተነስቷል:: ሁለቱ አገሮች ምርጫ እየተደረገባቸው ሲሆኑ ጭካኔና ጥቃት የሚታይባቸው በመሆናቸው ጥያቄ ውስጥ ወድቀዋል::

በአይቮሪኮስት ዋኛ ፖለቲካ ፓርቲ የሆነው በአገሪቱ ሊካሄድ የነበረው ምርጫ በመራጮች ምዝገባ ላይ በተከሰተው ፍራቻና ችግር ወደሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ ተስማምቷል::

በሐረሬ የተቃዋሚ መሪ የሆኑት ሚስተር ሞርጋን ቫንጋሪ በዚምባብዌ በተደረገው ምርጫ ተጭበርብሬያለሁ እያሉ ሲሆን የኦባማ ማሸነፍ ለየት ያለ «የፖለቲካ ብስለትና መከባበር» መኖር እንደሚገባው አስተምሯል ብለዋል::

ደጋፊዎቻቸው ሞተው ድል ከተቀዳጁ በኂላ በሮበርት ሙጋቤ ችግር እየተፈጠረባቸው ያሉት ሚስተር ቫንጋሪ የአሜሪካን ምርጫ አስመልክተው በተናገሩት ቃል «የዚምባብዌ ሕዝብ ትክክለኛ የሆነ ምርጫን ዋጋ አድንቋል ብዙ ዋጋ የተከፈለበት ነፃና ፍትሓዊ ምርጫና ውጤቱም በሁሉም ዘንድ የተከበረ ነው» በማለት ገልፀዋል::

# ሰብዓዊ መብቶች

Initiative africa

ኢሕባማ EBA

## የሰብዓዊ መብቶች ሁሉአቀፍ መግለጫ (እ.አ.አ. 1948)

እ.አ.አ. በ1945 የፀደቀውና የተፈረመው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ሰብዓዊና መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶች የሚከበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸትን እንደአንድ ዓላማው አድርጐ ተቀብሏል:: ኢሊኖር ሩዝቬልትን፣ ሬኔ ካሲን፣ ቻርለስ ማሊክን፣ ፔንግ ቸን ቻንግን እና ጆን ኸምፍሬን የመሳሰሉ እውቅ ሰዎች ባደረጉት ጥረትና ማበረታታት መንግሥታት ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ ሲከበሩላቸው ለማገቡ መብቶችና ነፃነቶች በአንድ ወጥ ሰነድ እውቅና ሲያገኙ እንደሚገባ ተገነዘቡ:: የዚህ ግንዛቤ ውጤትም እ.አ.አ ዲሰምበር 10 ቀን 1948 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ በሙሉ ድምፅ የፀደቀው «የሰብዓዊ መብቶች ሁሉ-አቀፍ መግለጫ» ሆኗ:: በዚህ ምክንያት በየዓመቱ ዲሰምበር 10 «የሰብዓዊ መብቶች ቀን» ሆኖ ይከበራል::

ይህ ሰነድ በሁሉም የሰው ልጅ የሕይወት ዘርፎች ያሉ መብቶችን የሚያካትት፣ «የሁሉም አገሮችና ሕዝቦች የጋራ ድል ነው::» በመጀመሪያ አንቀጹም «የሰው ልጆች ሁሉ ነፃና እኩል ሆነው ከክብርና ከመብት ጋር ተወልደዋል» ለማለው መሠረታዊ የመብት ማረጋገጫ መርህ እውቅና ሰጥቷል::

ሰነዱ በጥቅሉ በማናቸውም መልኩ የሚፈፀም መድልዎን የሚቃወም ከመሆኑም በላይ ሊከበሩ የሚገባቸውን ልዩ ልዩ የሲቪል፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ማኅበራዊ መብቶችን ይዘረዝራል:: ከአንቀጽ 3-21 ያሉት በፖለቲካ ስደተኝነት በሌሎች አገሮች ጠለላ የማግኘትንና የንብረት ባለቤትነት መብትን ጨምሮ ስነባር የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዕውቅና ይገልጣል:: ከአንቀጽ 22 እስከ 28 ያሉት የሰነዱ አንቀጾች ደግሞ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ መብቶችን ይደነግጋሉ:: ለምሣሌ አንቀጽ 28 «ማንኛውም ሰው በዚህ መግለጫ የተገለጡት መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ ለሚሆኑበት ማኅበራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት መብት አለው» ይላል::

የመግለጫው ስም እንደሚያመለክተው በቀጥታ የሕግ ተፈፃሚነት ያለው ስምምነት አይደለም:: ይሁንና አስፈላጊነቱ የሚናቅ አይደለም:: የመብቶች ጥሰት እጅግ ተስፋፍቶ በነበረበት በዚያ ወቅት ለሕዝቦች መብት ዕወቅና በመስጠት በአገሮች መካከል የተደረገ ስምምነት በመሆኑ ከፍተኛ የሞራል ተፅዕኖ አለው:: በሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች አጠባበቅ ረገድ ለቀጣይ ሥራዎች ጠንካራ መሠረት ጥሏል:: ከዚህም ባሻገር ሰነዱ ሁሉ-አቀፍ በሆነ መልክ የተለያዩ መብቶችን አጣምሮ የያዘ እንደመሆኑ የመብቶችን የጋራ ባህርያት፣ ተዛምዶና የእርስ በርስ መደጋገፍ አመላክቷል:: ይህም ከዓመታት በኋላ እ.አ.አ. በ1993 ኦስትሪያ ቪዬና ላይ በሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ የተካሄደው ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ባወጣው መግለጫ ተረጋግጧል::

*(Taken from "The United Nations Human Rights Treat System - An Introduction to the core human rights treaties and the treaty bodies, Fact Sheet No. 30).*

ሕጎቻችን

# የሕግ አስከባሪ ተቋማት

*ይህ ተከታታይ ጽሑፍ «አጠቃላይ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ሪፖርት» በሚል ርዕስ ከአቅም ግምባታ ሚኒስቴር የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ጽ/ቤት ካጠናቀረው ጥናት የተወሰደ ነው።*

## አቃቤ ሕግ

የአቃቤ ሕግ መ/ቤት የሕግ አስፈፃሚው አካል ሆኖ የተደራጀ ነው። የፌዴራል አቃቤ ሕግ ሥልጣን ለፍትህ ሚ/ር የተሰጠ ነው። ይሁን እንጂ የአቃቤ ሕግነት ሥራን የሚሠሩ ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶችም አሉ። በክልል መንግሥታት ደረጃም የሚገኙ የፍትህ ቢሮዎች እና የፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር ያለው ተግባርና ሥልጣን ተመሳሳይ ነው።

የፌዴራል አቃብያነ ሕግ የሚሾሙት በፍትህ ሚኒስትሩ በቀጥታ ወይም ሚኒስትሩ በሚያቋቁመው ጉባኤ ነው። በፌዴራል አቃቤ ሕግነት ለመሾም የሚቀርብ ዕጩ የሕግ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ሊኖረው ይገባል። አቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራን በሚመለከት ፖሊስን የመምራትና የማዘዝ ሥልጣን ያለው ሲሆን ከማረሚያ ቤቶች ጋር ግን ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት የላቸውም። የአቃቤ ሕግ ሥልጣን ሕጋዊ መሠረት እ.አ.አ. በ1957 የወጣው የወንጀል ሕግና በ1961 የወጣው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ናቸው። እነዚህ ሕጐች ቆየት ያሉ በመሆናቸው በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከጊዜው ጋር የማይሄዱ ናቸው። ይሁን እንጂ አዲሱ የሁለቱም ሕጐች የማሻሻያ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርቧል።

የፌዴራል የፍትህ ሚኒስትርም ሆነ የክልል የፍትህ ቢሮ ኃላፊዎች የዳኝነትና የአስፈፃሚነት ሥልጣን ደርበው የያዙ ናቸው። ይህ የሥልጣን መደራረብ የዐቃቤ ሕግ ነፃነትን የሚነጥቅ ሊሆን ይችላል። የዐቃቤ ሕግ ተግባር በተለያዩ አካላት የሚሠራ መሆኑና ይህን ሥራ የሚሠሩ አካላትም ለሌሎች አካላት ተጠሪ መሆናቸው ተቋሙን ሊያዳክመው ይችላል። ዐቃብያነ ሕግ የሚመረጡበትና የሚሾሙበት ሥርዓት ለሌላ ውጫዊ አካል ክፍት አይደሉም። ዐቃብያነ ሕግ ቁጥራቸውም አነስተኛ ነው። የሚሰጠውም ሥልጠና በቂ አይደለም። በተለይም በፖሊስ በሚከናወን የወንጀል ምርመራ ሥራ የዐቃቤ ሕግ ሚና እምብዛም አይደለም። የዐቃብያነ ሕግ የሥራ ሁኔታ አመቺ አለመሆንና የባለሙያ እጥረት የጉዳዮችን መጓተት እና የሥራ ጫና እያስከተለ ይገኛል። ዐቃብያነ ሕግ ከፍ/ቤት፣ ፖሊስና ማረሚያ ቤቶች ጋር ያላቸው የሥራ ግንኙነትም ዝቅተኛ ነው።

## ፖሊስ

የኢትዮጵያ ፖሊስ ተቋማዊ አወቃቀር በፌዴራልና በዘጠኙም የክልል መስተዳድሮች የተደራጀ ሲሆን በልዩ ሁኔታ የተደራጁ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ፖሊስ ተቋማትንም ያካትታል። የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲሆን የክልል መንግሥታት የራሳቸውን አደረጃጀት ለመከተል ይችላሉ። ሆኖም የክልል መንግሥታት የፖሊስ አደረጃጀት ከፌዴራል ፖሊስ ብዙም የተለየ አይደለም። የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽኖች ተጠሪነታቸው ለየከተማው አስተዳደር ነው። የፖሊስ ሥልጠና የሚካሄደው በፌዴራል ፖሊስ ኮሌጅና በየክልሉ ባሉ የፖሊስ ማሠልጠኛ ማዕከላት ነው።

የፖሊስ ተቋማዊ ጥንካሬ ከክልሎች ይልቅ በአዲስ አበባ የተሻለ ነው። ከፖሊስ ጐን ለጐንም በፈቃደኝነት የተደራጀ የአካባቢ ሚሊሺያ አለ። የሚመራውም በአስፈፃሚው አካል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አንድ የፎረንሲክ ላቦራቶሪ ብቻ ነው። ለፖሊስ የሚመደበው በጀት ውሱን ነው። ለምሳሌ በቂ ተሽከርካሪ የላቸውም። ችግሩን ለመቅረፍ ግን ጥረቶች ሲደረጉ ይታያል።

ሕብረተሰቡ በፖሊስ ላይ ያለው እምነት ዝቅተኛ ነው። ምንም እንኳን የፖሊስ አገልግሎት በሕዝብ ትብብርና ይሁንታ የሚከናወን መሆን እንዳለበት የተለያዩ ጥረቶች እየተደረገ ቢሆንም የፖሊስ አባላት አመለካከት ከወታደራዊ አስተሳሰብ የተላቀቀ አይደለም። በክልል ባሉ የፖሊስ ማሠልጠኛ ማዕከሎች የሚካሄደው ሥልጠናና የአሰለጣጠን ዘዴው ኋላ ቀር ነው። የአሰለጣጠን ዘዴው በፖሊስ ማሠልጠኛ ማዕከሎች ኋላቀርና ለውጥ የሌለው እንዲሁም ከሕብረተሰብ ፖሊሲንግ አስተሳሰብ ጋርም የሚጣጣም አይደለም። የፖሊስ ሕዝብ ጥምርታ (Population Police ratio) አጥጋቢ አይደለም። በተለይም ፖሊስ የአገሪቱን ብሔራዊ ወሰን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዲኖረው የሚደረግ ከሆነ የአቅም ውሱንነት ይኖራል። የገንዘብ እጥረትም አለ። የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ረገድም ያለው ሁኔታ እንዲሁ ውሱን ነው። በዚህም ምክንያት ውጤታማ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ መቀየስ አስቸጋሪ ሆኗል። የፖሊስ እንቅስቃሴ ውሱን ነው። የፖሊስ አካላት ብዙውን ጊዜ የፎረንሲክ ማስረጃን ከመጠቀም ይልቅ መተወን ይመርጣሉ። ምክንያቱም በአገሪቱ ያለው የፎረንሲክ ምርመራ ላቦራቶሪ አንድ ብቻ በመሆኑ ጥያቄውን ለማስተናገድ ስለማይችል ነው። የአካባቢ ሚሊሺያ ብዙም ቁጥጥር ሳይደረግበት የሚሠራበት አግባብና ሥልጠናም የሌለው መሆኑ አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ፖሊስ ከአቃቤ ሕግ ጋር ያለው ግንኙነት ዝቅተኛ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ዐቃቤ ሕግ የፖሊስን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚችልበት ሁኔታ ውሱን ነው።

ይህ እትም ለንባብ የበቃው በኢኒሼቲቭ አፍሪካ በኩል ከስዊድን ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።